OM OPPHOLDSTIDER, HENTE OG LEVERE,
SYKDOM OG FERIE I BARNEHAGEN
**AMHARISK**

# በመዋዕለ ሕጻናቱ ውስጥ የመቆያ፣ የመውሰድ እና የማድረስ፣ የህመም እና የእረፍት ጊዜ



## የመቆያ ጊዜ

አብዛኛውን ግዜ መዋዕለ ሕፃናት ከ07:30 እስከ 16:30 ድረስ ክፍት ናቸው። የተወሰኑ መዋዕለ ሕፃናት ከዚህ የተራዘሙ ክፍት ሰዓታት አላቸው። መዋዕለ ሕፃናቱ የየራሳቸውን የመክፈቻ ሰዓት ያሳውቋችኋል። ህፃኑ በመዋዕለ ሕፃናቱ ውስጥ በየቀኑ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበት የምትወስኑት እናንተ ናችሁ።

ብዙውን ጊዜ መዋዕለ ሕፃናቱ ከቀትር በፊት የእግር ጉዞዎች፣ የዘፈን ጊዜ፣ የቋንቋና የጨዋታ ቡድኖች እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ይኖራቸዋል። ወደ መዋዕለ ሕፃናቱ አርፍዳችሁ የምትመጡ ከሆነ ይህንኑ በቅድሚያ አሳውቁ። ይህን በማድረግዎ የመዋዕለ ሕጻናቱ ሠራተኞች የዕለቱን እንቅስቃሴ ለመጀመር ሕፃኑን መጠበቅ እንደሚኖርባቸውና እንደማይኖርባቸው ቀድመው ለማወቅ ይረዳቸዋል።

## ሕፃኑን ወደ መዋዕለ ሕፃናት ማድረስ እና መውሰድ

ወደ መዋዕለ ሕፃናቱ ሲመጡ ሕፃኑን በጥሩ ሁኔታ መቀበል እንዲቻል ሠራተኞቹን ያነጋግሩ። ህፃኑን ለመውሰድ ሲመጡ እና ከመዋዕለ ሕጻናቱ ወጥተዉ ሲሄዱ ለሠራተኞቹ ይንገሩ። ይህ ለሕፃኑ ደህንነት እንዲሁም ህፃኑን የሚመለከት መረጃ ለመለዋወጥ ይጠቅማል።

ከእናንተ ከሕፃኑ ወላጆች ውጪ ሌላ ሰው መጥቶ ህፃኑን የሚወስድ ከሆነ፣ ይህንን መዋዕለ ሕፃናቱ እንዲያውቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህ ሲሆን መዋዕለ ሕፃናቱ ለሕፃኑ አስቀድሞ በማሳወቅ ማዘጋጀት ይችላል። ከዚህ በተረፈ የቅድሚያ ስምምነት ሳይኖር፣ ሕፃኑ ራሱ የሚያዉቀዉ ሰዉ እንኳን ሊወስደዉ ቢመጣ፣ መዋዕለ ሕጻናቱ ሕፃኑን ለሌላ ሰው መስጠት አይፈቀድለትም።



© Trude Haugen







### እረፍት እና ነጻ ቀናት

በዓመት ውስጥ ክፍያ የማይጠየቅባቸዉ አራት ሳምንታት አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አምስቱ ቀናት የእቅድ ማውጫ ቀናቶች ሲሆኑ በነዚህ ቀናቶች ህፃናቱ ነጻ ናቸው። የተቀሩት ሦስት ሳምንታት ለዓመት እረፍት የሚውሉ ናቸው።

አንዳንድ መዋዕለ ሕፃናት ሙሉውን የበጋ ጊዜ ክፍት ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ለዓመት እረፍት ሲባል ከሁለት እስከ ሦስት ሳምንታት ያክል ይዘጋሉ። ብዙውን ጊዜ መዋዕለ ሕፃናቱ ህፃኑ የበጋ (የዓመት) እረፍት መቼ እንደሚወስድ ወላጆች እንዲያሳውቋቸው ይጠይቃሉ። ሕፃኑ በበጋ (በዓመት) እረፍቱ ወቅት ወደ መዋዕለ ሕፃናቱ መምጣት አይችልም። ከተስማማችሁበት የእረፍት ሳምንታት ውጪ፣ ሕፃኑ ነፃ እረፍት የሚወስድ ከሆነ መዋዕለ ሕጻናቱን ማሳወቅ ይኖርባችኋል።

በክብረበዓላት ቀን እና ሜይ 17 ቀን መዋዕለ ሕፃናት ዝግ ናቸው። አብዛኞቹ መዋዕለ ሕፃናት ከገና በዓል፣ ከፋሲካ፣ እንዲሁም ከትምህርት ቤቶች የክረምትና የፀደይ ወቅት እረፍት ጋር በተያያዘ ሕጻናት እረፍት ይወስዱ እንደሆን ለማወቅ ወላጆችን ይጠይቃሉ። ይህ መረጃ በነዚህ ቀናት ምን ያህል ሕጻናት ወደ መዋዕለ ሕጻናቱ እንደሚመጡ ለማወቅና ለሰው ኃይል ምደባ እቅድ ለማውጣት ይረዳቸዋል።

### ህመም

የሕጻኑ አጠቃላይ የጤና ሁኔታ ጥሩ ካልሆነ ወደ መዋዕለ ሕፃናት ሳይመጣ ከቤት መቆየት አለበት። ጥሩ ያልሆነ አጠቃላይ የጤና ሁኔታ ሲባል ከልክ ያለፈ የድካም ስሜት፣ የማቅለሽለሽና የአቅም እጦት ወይም የምግብ ፍላጎት መዘጋት ሊሆን ይችላል። ትውከትና ተቅማጥ ያለባቸው ሕጻናት፣ የትኩሳት ስሜት ባይኖራቸውም፣ የሕመሙ ምልክት ከጠፋም በኋላ፣ ለሁለት ቀናት ቤት ውስጥ መቆየት አለባቸው።

ሕጻናት ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ማድረግ የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት በሽታው በመዋዕለ ሕፃናቱ ውስጥ እንዳይዛመት ለመከላከል ነው። ከዚያም አልፎ ሕፃኑ ተጨማሪ እንክብካቤ ስለሚያስፈልገው እና መዋዕለ ሕፃናቱ ለታማሚው ሕፃን አንድ ሰው ለብቻው መድቦለት ለመንከባከብ አቅም ስለሌለው ነው።

ሌሎች ሊተላለፍ በሚችል በሽታ ተይዞ ከሆነ ደውሎ መንገሩ የበለጠ አስፈላጊ ነው።

## የመድሀኒት አሰጣጥ

አንዳንድ ጊዜ ሕጻናት ከበሽታቸው ለመዳን መድሀኒት ያስፈልጋቸዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ሀኪም በሚያዘው መሠረት መድሀኒቱ በትክክለኛው መንገድ እና በትክክለኛው ሰዓት መስጠት የወላጆች ኃላፊነት ነው። መዋዕለ ሕፃናቱ መድሀኒት የመስጠት ግዴታ የለበትም፥ ነገር ግን ህመም ሲከሰት መድሀኒት በመስጠት ረገድ አብዛኛውን ጊዜ ይተባበራል። ይህን ለማድረግም በቅድሚያ ከመዋዕለ ሕፃናቱ ጋር መስማማት ያስፈልጋል።

አንዳንድ ሕፃናት ስር ሰደድ በሽታ ስላለባቸው በየቀኑ መድሀኒት መውሰድ ይኖርባቸዋል። መዋዕለ ሕፃናቱ ይህን አይነት መድሀኒት እንዲሰጥሎት ከፈለጉ፣ አስቀድመው ማነጋገር ይኖርቦታል። ይህ ሲሆን ሠራተኞቹ መድሀኒት እና አሰጣጡን በተመለከተ አስፈላጊውን ትምህርት ማግኘት አለባቸው።




BERGEN KOMMUNE

Foto forside: © Asle Bentzen
Skipnes.no Svanemerket trykksak, 2041 0731